የሰበር መ/ቁ. 20954

ቀን 25/9/98

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- የኦሮሚያ ብድርና ቁጠባ አ.ማ. ጠበቃው ቀርቧል።

መልስ ሰጭ፡- አቶ ጌታቸው ግርማ ቀርቧል።

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር አንድ ሠራተኛ ከሥራ የተሰናበተው በህገ ወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ሥራ እንዲመለስ በአዋጁ ቁ. 42/85 መሠረት ሲወሰን ከሥራ ከተሰናበተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለስ ውሣኔ እስከተሰጠበትና ሥራ ላልተሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል? ወይም አይገባም? የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ነው።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የሥር ፍ/ቤት መ/ሰጭ ከሥራ የተሰናበተው በሕግ ወጥ መንገድ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ሥራው እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን ውሣኔውን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አጽንቶታል። አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 1/10/98

ችሎቱም አንድ ሠራተኛ ከሥራ የተሰናበተው በሕገ ወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሲወሰን ከሥራ ከተሰናበተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ሥራ እንዲመለስ ውሣኔ እስከተሰጠበትና ሥራ ሳልተሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊፈለው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ነጥብ መሠረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል።

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 17189 አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁ. 42/85ን ድንጋጌዎች በመተርጎም ሕጉ ሥራ ሳልተሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚፈቅድ አይደለም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል። በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ለመ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

## ው ሣ ኔ

- ይህ ችሎት መ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዙ ሊከፈል አይገባም በማለት ወስኖ የባሌ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 232/95 በ13/9/96 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 11911 ሐምሌ 11 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 1/10/98